# ፍትሕ ለኢትዮጵያ ግብረ ኃይል

## ጋዜጣዊ መግለጫ

## መንግሥቱ ኃይለማርያም ለፍርድ ሊቀርብ ነው!

በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ እጅግ መራር የሆነ መጠነ ሰፊ ግፍና ያልተቆጠበ ወንጀል ፈጽሞ የሕዝቡ ቁጣ ሲገነፍል ሀገር ጥሎ በመሸሽ ዚምባብዌ በምትባል ሀገር ተሸሽጎ የሚገኘው፣ የደርግ አገዛዝ መሪ የነበረው መንግሥቱ ኃይለማርያም ለፍርድ እንዲቀርብ ተጨባጭ እርምጃ እየተወሰደ ነው።

“ፍትሕ ለኢትዮጵያ ግብረ ኃይል” በመሰኘት በቅርቡ በአሜሪካ ሀገር የተቋቋመው ሕዝባዊ ድርጅት በጉዳዩ የሚያምኑ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች የሚሳተፉበት ድርጅት ሲሆን ዓላማውም ማንንም ሥልጣኑን ተገን አድርጎ የሰው ሕይወት ያጠፋን ለፍርድ ለማቅረብ ሲሆን የመጀመሪያ ጥረቱ የሚያተኩረው መንግሥቱ ኃይለማርያምን ለፍርድ ማቅረብ መሆኑን አረጋግጧል።

የግብረ ኃይሉ ራዕይ ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለሰብአዊ መብት መከበር፣ ለሰላም፣ ለአንድነት በኢትዮጵያዊነት፣ ቀጣይ ለሆነና ለመላው ሕዝብ ለሚደርስ ልማት ባለማሰለስ የሚጥር አመራር በተግባር ላይ ውሎ ለማየት ነው። ዓላማውም የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ተከስቶበት ከነበረው የአምባገነን አገዛዝ ለመላቀቅና ለዴሞክራሲ ሥርዓት የጀመረውን ትግል በማኮላሸት መንግሥቱ ኃይለማርያም ለፈጸማቸው እጅግ ብዙ ወንጀሎች ለፍርድ እንዲቀርብ በማድረግ ለወደፊቱም ማንኛውም ተመሳሳይ ግፍ የሚፈጽም የኢትዮጵያ መሪ ተጠያቂ እንደሚሆን ግልጽ መልእክት ለማስተላለፍ ነው።

እንደሚታወቀው፣ በደርግ 17 ዓመትና በኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራቲክ ግንባር (ኢሕአዴግ) 25 ዓመት ዘመነ ግፍ አገዛዝ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ተጨፍጭፈዋል። ከነሱ ውስጥ አብዛኛዎቹ ወጣቶችና ሴቶች እንደ ነበሩ የታወቀ ሐቅ ነው። እንዲሁም፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት የአመራር አባላት ከነበሩት ውስጥ 57 ባለሥልጣኖችን ያለአንዳች የፍትሕ ሒደት፣ መንግሥቱ ኃይለማርያም በራሱ ፊርማ ወስኖ ያስገደለ መሆኑ በይፋ የታወቀ ነው። በኢትዮጵያ ታሪክ፣ እንደ ከፍተኛ ሰቆቃ ምን ጊዜም የማይዘነጋው፣ በመንግሥቱ ኃይለማርያም አመራር የተከናወነው የ“ቀይ ሽብር” እልቂት ነው። በዚሁ እጅግ አሳዛኝ ጭፍጨፋና የስቃይ ዘመቻ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን ሰለባዎች እንደ ነበሩ የታወቀ ነው። እስካሁንም ድረስ ብዙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች በ“ቀይ ሽብር” ጠንቅ በተጨፈጨፉባቸው የቅርብ ዘመዶችና ወገኖች ኃዘናቸው አልለቀቃቸውም። በተጨማሪም፣ በመንግሥቱ ኃይለማርያም አመራር፣ በደርግ አማካኝነት እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን በእስር፣ በወከባ፣ በድብደባና በሌሎች ልዩ ልዩ ጥቃቶች እንደ ተሰቃዩ የተረጋገጠ ነው።

ከላይ ከተጠቀሱት የደርግ ወንጀሎች በተጨማሪ፣ በኢትዮጵያ ላይ ተከስቶ የነበረው ኢዴሞክራሲያዊ የሆነ መራር የነበረ ከልክ ያለፈ አምባገነንነት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ያመነመነ፣ ጸጥታዋን ያደፈረሰና የርስ በርስ ግጭት ያመቻቸ ነበር። በዚህም ምክንያት በልዩ ልዩ አካባቢዎች የተቀሰቀሱት ተቃውሞዎችና ውጊያዎች ሀገሪቱን ለከፋ እልቂትና መገነጣጠል ዳርገዋታል። ከሶማሊያ ጋር የተከሰተው ግጭትና በኤርትራም የተከናወነው ጭፍጨፋ ለሀገሪቱ መከፋፈልና እልቂት አንደኛው ምክንያት የመንግሥቱ ኃይለማርያምና የደርግ ደካማና ብልሹ አመራር እንደ ነበር የታወቀ ነው።

በመንግሥቱ ኃይለማርያም አምባገነናዊ አመራር በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ላይ ለደረሰው ወንጀል ዋናው ተጠያቂ እሱው በመሆኑ ለፍርድ ማቅረቡ ታሪካዊ ግዴታ ነው። እስካሁንም ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ልባዊ ይቅርታ በመጠየቅ ፋንታ አጉል ጀግንነት የተንጸባረቀባቸው ጽሑፎችና መልእክቶች ማስተላለፉ አንዳችም የሕሊና ጸጸት ያልታሰማው መሆኑ ግልጽ ነው።

ስለዚህ መንግሥቱ ኃይለማርያም ለፈጸመው ወንጀል ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርብ “ፍትሕ ለኢትዮጵያ ግብረ ኃይል” በቸሩ የኢትዮጵያ አምላክ እርዳታ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ ቆርጦ ተነስቷል። ለዚህም የተቀደሰ ተግባር ለሀገር ፍትሕ የሚቆጩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ እርዳታቸውንና ድጋፋቸውን እንዲለግሱ በትሕትና ያሳስባል።

ግፈኛው መንግሥቱ ኃይለማርያም ከፍትሕ አያመልጥም!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!
ኢሜል ፡ FEG012009@gmail.com
መስከረም 21 ቀን 2009 ዓ.ም.